ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ዕድገት (የወተት አምራች አርሶ አደሮች) ፕሮጀክት

# የጥጆች አያያዝ መመሪያ



ጥጆችን ተንከባክቦ ማሳደግ የወተት ልማቱን ጠንካራ መሠረት ላይ ማስቀመጥ ነው!

SNV

# ኤስ ኤን ቪ. ኢትዮጵያ ዕድገት (የወተት አምራች አርሶ አደሮች) ፕሮጀክት

**1**

ጥጆችን ተንከባክቦ ማሳደግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ምርት ለመስጠት የሚችሉ የወተት ላሞችን ለማግኘት ይረዳል፡፡

**2**

- ጥጆች እንደተወለዱ እናቶቻቸው በምላሳቸው በመላስ በጥጆቹ ላይ የሚገኘውን ዕርጥበት ለማስወገድ እንዲችሉ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡
- ይህ ካልተቻለ በጆንያ (ጨርቅ) ወይም በንጽህና በተያዘ የሳር ድርቆሽ ማድረቅ ይቻላል፡፡
- ከሶስት እስከ ስድስት ሰዓት ለሚሆን ጊዜ እንዲጠቡ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡

**3**

ጥጆችን በተወለዱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ እንገር ማጠጣት ይገባል፤ ይህም የበሽታ መከላከል አቅም እንዲፈጠር ይረዳል፡፡

1



2



3



# ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ዕድገት (የወተት አምራች አርሶ አደሮች) ፕሮጀክት

**4**

ጥጆችን ከወተት ማጠጫ እቃ እንዲጠጡ ለማስተማር፡-

- እጅን በጥንቃቄ ታጥቦ ጣትን በወተቱ ውስጥ በመንከር እንዲጠቡ ማድረግ
- ቀስ በቀስ የሚጠቡትን ጣት እየተከተሉ ወደ ወተት ማጠጫው ዕቃ እንዲጠጉ በማድረግ የሚጠቡትን ጣት ወተት ውስጥ በመንከር ጣትን በመጥባት ላይ እያሉ ወተቱን መጠጣት እንዲጀምሩ ማድረግ ነው፡፡

**5**

- ጥጆች ከተወለዱ እስከ ሶስተኛው ወር ድረስ ቀስ በቀስና በትንሽ በትንሹ ወተት እንዲጠጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ከአንድ ሳምንት በኋላ ለምለም ሳር በመስጠት ቀስ በቀስ መመገብን ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡

**6**

ጥጆች አንድ ሳምንት ከሞላቸው በኋላ ንጹህ ውሃ በንጹህ እቃ መስጠት ይገባል፡፡

**7**

ጥጆች የበለጠ ጤናማ እንዲሆኑ ቀስ በቀስ የተመጣጠነ ድብልቅ መኖ በመስጠት ማለማመድ ይገባል፡፡

4



5



6



7



# ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ዕድገት (የወተት አምራች አርሶ አደሮች) ፕሮጀክት

8

የጠነከሩና የሚሰጣቸውን ሳርና ሌሎችንም መኖዎች በሚገባ በመመገብ የተሟላ ጤንነት ያላቸውን ጥጆች በሦስተኛ ወር ዕድሜያቸው ወተት አለመስጠት ይቻላል፡፡

9

ለጥጆች ውሃና ወተት የሚጠጡባቸውን እቃዎች በንጽህና እንዲያዙ በማድረግ የጥጆችን ጤንነት መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

10

- ጥጆች ርጥበት በሌለው፡ ንጹህ፡ ነፋሻና በቂ ብርሃን የሚገባበት ማረፊያ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ለጥጆች የሚሰሩ መቆያዎች ወርድና ርዝመት አንድ ሜትር በአንድ ሜትር ተኩል በሆነ እንጨት መሠራት አለባቸው፡፡
- የጥጆቹ መቆያ ውስጥ ድርቆሽ ሳር መጎዝጎዝ ሙቀት እንዲያገኙ ይረዳል፡፡

11

መመገብያው ጥጆቹ በፈለጉ ጊዜ ለመመገብ እንዲችሉ ከመቆያ ቦታቸው ላይ የመኖ ሳር ማቅረቢያ ሊደርሱበት በሚችሉበት ከፍታ መሠራት አለበት፡፡

8




9



10



11



# ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ዕድገት (የወተት አምራች አርሶ አደሮች) ፕሮጀክት

**12**

- ለጥጆች ዕድገት የፀሐይ ብርሃን አስፈላጊ ነው፡፡
- ስለዚህ ጥጆች በተወሰነ ቦታ ተለቀው እንዲዝናኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**13**

ጥጆች በቂ የህክምና ክትትል እንዲያገኙ እና በወቅቱ እንዲከተቡ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

**14**

ጥጆች በውስጥ ጥገኛ በሽታ በቀላሉ እንዳይጠቁ በንጽህና የተያዘ እንዲሁም የከብቶች እበትና ሽንት የማይበክለው መመገቢያ በማዘጋጀት እንዲመገቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**15**

ጥጆች ወተት መመገብ ካቆሙ በኋላ ለጥጆች ብቻ በሚከለል የግጦሽ ቦታ ተሰማርተው እንዲግጡ ማድረግ ጤንነታቸው እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

12



13



14



15



# ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ዕድገት (የወተት አምራች አርሶ አደሮች) ፕሮጀክት



ጥጆችን
ተንከባክቦ ማሳደግ
የወተት ልማቱን ጠንካራ
መሠረት ላይ ማስቀመጥ ነው!

CAF PRINTING PRESS 0911 644726

T:+251(0) 11 126 21 00 P.O.Box 40675 W: www.snvworld.org

SNV